*በምርኮኛ መጽሐፍ ላይ የግል አስተያየት*
*ከ፡* ***<u>ነሲቡ ስብሐት</u>*** <u>(USA)</u>
***ቀን፡ ጥቅምት*** 19, 2003 (October 29, 2010)

***ውድ አንባቢያን፡*** *ይህንን ጽሁፍ ከማንበባችሁ በፊት በቆንጂት ብርሃን*, 2002 *ዓ.ም. የተጻፈውን "ምርኮኛ" መጽሐፍ ብታነቡ ይመረጣል። ምናልባት መጽሐፍ የማንበብ ሞራላችሁ ዝቅ ያለ አንባቢያን የመገፋፋት፡ የመነሳሳት፡ ጥንካሬ ማግኘት ከፈለጋችሁ አንብቡትና ከዚያ መጽሐፉን ልታነቡት ትችላላችሁ።*

## ***ቆንጂት ብርሃን*** አስነበበችን

*በአንድ ብዕር ሁለት መጽሐፍ። የዚያን ትውልድ ተጋድሎና የዘመኑን መቅሰፍት። በአንድ በኩል በወጣትነት ዘመኑ ያ ትውልድ ለህገሩ አንድነት፡ ለሰው ልጆች መብትና ለዴሞክራሲ ያደረገውን ተጋድሎና የከፈለውን መስዋዕትነት፡ በሌላ በኩል የዛሬው ወጣቶች ደግሞ በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተጠቁትን ወገኖች በግብረ ሰናይ ድርጅቶች አማካይነት የሚያደርጉትን እንክብካቤና ሕይወት አርዝም ጥረት።*

*ቆንጂት ብርሃን "ለልጆች የሚደርስ አደራ" አስነብባናለች። አደራዋን ሳትበላ የገባችውን ቃል ተወጥታለች። ቃል ኪዳኗን አክብራለች። የፍርዬን አደራ ለሕዝብ አበርክታለች። ሕይወት ዘርታበታለች። እነዚያ ብርቅዬዎች ከመቃብር በላይ ከፍ ብለው እንዲታዩ አድርጋለች። ዛሬም ታሪካቸው ተናፋቂና ህያው እንደሆነ አስነብባ በበኩሌ አስለቅሳኛለች። "ምነው የረሳነውን ታስታውሽናለሽ? ለምን ቁስላችንን ትቀሰቅሻለሽ? ምናለ ብትተይን?..." ያሏትን ሁላ ሳትሰላችና ተስፋ ሳትቆርጥ ትዕግስትን ተላብሳ ተወጥታዋለች። በአንጻሩም "ምን እንርዳሽ? በርቺ፡ ይህን አስተካክይ..." እያሉ ለብዕሯ ቀለም የሆኑትን እያመሰገነች ባካፈለችን ውርስ ያትውልድ ይመርቅሽ፡ ይህ ትውልድ ያክብርሽ እላለሁ።*

*ምርኮኛ ዋና ገጸ ባህሪ ፍሬህይወትን አድርጋ የቤተሰቡን በጋራ በአንድ ዓላማ መቆም ሲያመላክት በደረሰው ፈተና ደግሞ የተለያዩ ገጠመኞችን አካቷል። የወ/ሮ ስርጉት ለልጆቻቸው ካላቸው ፍቅርና እንክብካቤ በተጨማሪ ልጆቻቸው የተከተሉትን ዓላማና ጽናት ከማድነቅ ባሻገር አንዳንዴ እራሳቸውም ሳያስቡት ልጆቻቸው የሚነግሯቸው ይመጣባቸውና "...ያለም መሠረት አዲስ ይሁን ኢምንት ነን እልፍ እንሁን..." እያሉ የልጆቻቸውን ሁኔታ ይቃኛሉ። በወቅቱ በተለይ ወላጆች የመከራው ቀማሽና ተሸካሚ እንደነበሩ ወ/ሮ ስርጉትና የበላይሁን አባትና እናት ያሳዩናል። በአካባቢዋ በመጋለጥ ከአ.አ. መውጣት የተገደደችው ሚሚ "ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ፤ እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቸጉቬራ..." ብላ ወደ አሲምባ ተጉዛ እስከዛሬ የት እንደደረሰች አለመታወቁ የብዙ ቤተሰቦች ጥያቄና እየዬ ነው። የቃለአብ ታስሮ በቀይሽብር መገደልና ወላጅ እናቱ ይዘው የሄዱት ምግብ ከተጨማሪ ልብስ ጋር ሲመለስላቸው፡ በጠራራ ጸሐይ በስርቤቱ በራፍ መርዶ ሲነገራቸው የፈጠረው ሁኔታ የብዙ እናቶች አባቶች ቁስል ነው። የወንድምና የእህቶቹን ፍቅር ሳይጠግብ ሁሉም ከአጠገቡ ተለይተውበት ለስደት የበቃው ሮቤል በልጅነቱ የተቀረጸበትን ስነልቦናዊ ቁስል የሚጋሩ ብዙዎች ናቸው። ይህ ቤተሰብ ዛሬ የለም። ቤቱ ተዘግቷል። ሮቤል ቤቴ ብሎ መግቢያ የለውም። ስንቶቻችን የዚህ ታሪክ ባለቤቶች እንሆን?*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ምርኮኛ ከዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ተነስቶ፣ በተፋፋመው የመብትና ዴሞክራሲያዊ ትግል አስጉዞ የነበረውን ግፍና መከራ ተርኮ፣ የሕይወት እንደገናን አስመርኩዞ የሁለት ጦርነቶች ምርኮኛ ስለሆነችው ፍሬሕይወት ሲያስነብበን በየመሀሉ በርካታ ቁም ነገሮች ሊሠመርባቸው እና ሊደምቁ የሚገቡ ሀሳቦችን አስቀምጦልናል። ምስጋና ለመምሬ ብርሃን ልጅ ይግባትና የስነጽሁፍ ሰው ባልሆንም በመጽሐፉ ውስጥ የታዩኝንና የገቡኝን፣ ስሜቴን የነኩትን ላካፍላችሁ ወደድሁ።

## ➢ <u>የምርኮኛ አንዳንድ አገላለጾች</u>

*የሕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻን ጉዞ አስመልክቶ ገጽ 38፤*

***አምስት ኪሎ የዘመቻ መምሪያው ግቢ በዘማቾችና በሸኚዎች ተጨናንቋል። እዚህም እዚያም ሸኝና ተሸኝ እየተቃቀፉ ይላቀሳሉ። ምድር ቀውጢ ሆናለች። አውቶብሶቹ በራቸውን ከፍተው ይጠባበቃሉ። አንዱ ስለሌላው ምንም ደንታ የለውም፤ ሁሉም በየራሱ ጉዳይ ተጠምዶ ወዲያ ወዲህ ይላል…"ዘማቾች ወደ መኪናዎቻችሁ እንድትገቡ ትጠየቃላችሁ" የሚለው ድምጽ ተደጋገመ።…መኪናው ሞተሩን አሞቀ ተነሳ። በአውቶብሱ መስኮቶች አንገታቸውን አውጥተው የመጨረሻ ስንብት ለማድረግ ተረባረቡ ዘማቾቹ።…***

*የጀማን ወንዝ አስታካ ስለ ተፈጥሮ በምርኮኛ ከቀረበው፤*

*ገጽ 63 **ከሜዳው አለፍ ብሎ ያሉት ጉብታዎች ላይ ወጥቶ እስኪቀመጥና ቆላውን ማየት እስከሚችል ይቸኩላል። እዚያ ሲደርስ ደስታው ይጨምራል፤ ተመቻችቶ ይቀመጥና ዐይኖቹን በርቀት ወዳለው የትላልቅ ተራሮች ሰንሰለት ይልካቸዋል። ከተራሮቹ በስተግርጌ ያለው ረጅም ገደል ኀበዝ መሀንዲስ የነደፈው ሕንፃ ይመስላል። ከገደሉ አናት ላይ እየተወረወረ የሚንቧቸው ውሀ ድምጹ ባይሰማውም ዕይታው ብቻ መንፈሱን ያማልለዋል። ፏፏቴው ተወርውሮ ከሚያርፍበት ባሕር ረጋ ብሎ ስርዓት ባለው መልኩ እየፈሰሰ ከትልቁ ወንዝ ጋር ይቀላቀላል። ትልቁ የጀማ ወንዝ ከየሥፍራው ገባሮቹን እየተቀበለ በስፌ መልካው ያካትትና በእርጋታ ሲጓዝ በርቀት ለሚመለከቱት የበላይሁን ዐይኖች ረጅም መቀነት ይመስላል።***

*ምርኮኛ የኢሕአፓን ልሳን ዴሞክራሲያን በዚህ መልኩ ገልጻዋለች፤*

*ገጽ 58 "…**ገልመጥ ገልመጥ አለችና ወረቀቱን ከጉያዋ አወጣችው። ያየችውን ማመን አቃታት ግራ ገባት፣ ቢሆንም ማንበብ ጀመረች። ከወረቀቱ አናት ላይ በትላልቅ ፊደላት በቀይ ቀለም የተጻፈው "ዴሞክራሲያ" ይላል። አንብባ ባታውቅም ስለዚህ ወረቀት ሰምታለች። ልቧ መዝለል ጀመረች።…" ገጽ 60"… <u>ከማይነጥፍ የፖለቲካ ዕውቀት ምንጭ ለሚጨለፉትና</u> በየእትሙ ለሚወጡት ጽሁፎች የምትሰጠው ግምት ከምንም በላይ ሆነባት። ዴሞክራሲያን የሚጽፉት ሰዎች ይደንቋታል፤ በየጊዜው የሰው ስሜት የሚሰርቁ የተለያዩ ጽሁፎችን የመጻፋቸው ነገር እጅጉን ይገርማታል።…"***



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በወቅቱ ዝነኛዋ መጽሔት ኅህ በምርኮኛ አገላለጽ

ገጽ 104 "..."**ኅሕ" ማለት ተወዳጁ የጊዜው መጽሔት ነው። ኅሕን አግኝቶ ሳያነብ የሚያስቀምጥ ማን አለ? ጥቂት ከቆየ እንደሚወሰድና ላይመለስ እንደሚችል ስለሚገመት እጅ ከገባ ማንበብ ነው። በኅሕ መጽሔት ላይ ምን የማይወጣ ነገር አለ? ምን የማይተነተን የፖለቲካ ጉዳይ አለ? ትረካዎቹና ልቦለዶቹ ልብን ይነካሉ፤ ግጥሞቹ ስሜት ይቀሰቅሳሉ፤ ትንታኔዎቹ ዕውቀት ያስጨብጣሉ።**..."

ኢሕአፓ የህዝብ ድርጅት እንደመሆኑ የእንቅስቃሴውም የገቢ ምንጭ ውድ አባላቱ እንደነበሩና ያላቸውንም መተሳሰብ ቆንጂት በብዕሯ ይህን ትላለች፤

ገጽ 118 "**ለድርጅታቸው የሚገባውን ወርሀዊ መዋጮ ለመክፈል አስታዋሽ አያስፈልጋቸውም። ድርጅታቸውን ለማጠናከር የሚገባውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ የሚል የለም። ማንኛቸውም የግል ገቢ የላቸውም፡ ከቤተሰብ እንኳ በቋሚነት የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ አያገኙም፤ ግን እንደምንም ብለው በምንም መንገድ ያገኟትን ሳንቲም አጠራቅመው፡ አሮጌ ልብሶችና ጫማዎቻቸውን ሸጠው፤... ያገኟትን ለድርጅታቸው መስጠት ከምንም በላይ ያረካቸዋል። እርስ በርሳቸው ያላቸው መተሳሰብ ልዩ ነው። አንዳቸው ለሌላው ህይወታቸውን እንኳ ቢሆን እስኪሰጡ ድረስ ፍቅራቸው የጠነከረ ነው።**"

## ➢ የመገናኛ ዘዴዎች

በኢሕአፓ የመገናኛ ኮድ ዘዴ፡ ጥንቃቄና ፈጠራን ያካተተ ነው። ፍርዬ ተመልምላ የመጀመሪያ ግንኙነትዋን በዚህ መልክ ነበር ምርኮኛ ያስነበበችን፤

ገጽ 111 "**መፋቂያሽ ከየት ተላከልሽ?" አላት እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ። ደንገጥ ብላ እጇን ከኪሷ አወጣችና፤**

**"ከጃይማካ" ብላ ጨበጠችው**

ፈጠራን የተላበሰው የመገናኛ ዘዴ

ገጽ 178 **ቀጠሮዋ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ነው። አለባበሷም ቦታውን እንዲመስል ተደርጓል። ጥቁር ጥለት ነጠላዋን ንጥል አድርጋ ለብሳና ጥቁር ሻሽ ሸብ አድርጋ የሰኔ ጎልጎታዋን ገልጣ ከቤተክርስቲያኑ በር በስተቀኝ ካለው ስዕል ፊት ተቀመጠች። ወዲያውኑ ሰፋ ያለ ኮት የለበሰና ካኪ ሱሪ ያደረገ ሰው ኬፑን አውልቆ ሁለት ጊዜ ተሳለመና ወደእርሷ ዞረ።**

**"ምልኩስናሽ ዛሬ ነው?" አላት ኮስተር ብሎ።**

**"ኧረ ጋብቻዬ ነው" አለች። ሰውየው አጠገቧ ተቀመጠ።**



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

*ወደ ስደት፣ ወይም ለድርጅታዊ ጉዳይ ወደ ሌላ አካባቢ ሲኬድ ከአድራሽ ጋር የነበረ ግንኙነት፣*

*ገጽ* 213 ***"አዝመራውን ማን ይጠብቃል?" አላት አንድ ሰው መኪና ተራው ውስጥ ገብታ ጥቂት እንደቆመች።***

***"እረኞቹ" አለችው ደንገጥ ብላ። ወንበር እንደተያዘላት ነገራትና ተከትላው ወደመኪናው ውስጥ ገባች።***

*የፓርቲው ንብረት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ሲጓጓዝ ከነበሩት ትውስታዎች ምርኮኛ ያቀረበችልን፤*

*ገጽ* 296 ...***የምትወስጂውን ዕቃ እዚች መኪና ውስጥ ታገኛለሽ፣ መኪናው ሲያወርድሽ ዕቃውን በጀርባሽ ተሸክመሽ በግራ በኩል ያለውን መንገድ ተከትለሽ መስቀለኛ መንገድ እስከምታገኝ ድረስ ትሄጃለሽ። የቀኙን ቅያስ ተከትለሽ ጥቂት ስትራመጂ የሚጠብቅሽ ሰው አለ፤ የያዝሽውን ዕቃ ነካ አድርጎ "ወፍጮ ቤቱን ታውቂዋለሽ?" ይልሽና መልስ ሳይጠብቅ ይሄዳል ተከተይው፤ ዕቃውን ይቀበልሻል። ዕቃውን ከሰጠሽው በኋላ በመጣሽበት መንገድ አትመለሽም፤ ወደፊትለፊት ስትሄጂ ታክሲ መሳፈሪያ ታገኛለሽ የምታውቂውን ቦታ የሚጠራ ታክሲ ተሳፍረሽ ወደቤት ትመለሽ" አላት።***

*የኢሕአፓ የህቡዕ እንቅስቃሴ እንዴት ጠንካራ እንደነበርና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያካተተ መሆኑ ታሪክ ምስክር ነው። ነብሳቸውን ይማርና የካዛንችሷ እማማ ወደ ገበያ የሚሄዱ በማስመሰል የድርጅቱን ዶክመንቶች በዘምቢላቸው ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው በማጓጓዝ የሚያደርጉት እገዛና የቤት ሠራተኛዋ ደመቀች ታሪክ ከምርኮኛ ባለታሪኮች እመቤትና ሚስጥረ ተያያዥነት ያለው እውነተኛ ታሪክ ብዕር ይፈልጋል።*

- ***<u>የሴቶች ተሳትፎ በምርኮኛ</u>***

*ኢሕአፓ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ሴቶች እህቶቻችን በድርጅቱ ተሰልፈው መብታቸው ተከብሮ፣ ሚናቸው ታውቆ፣ ጀግንነታቸው ተደንቆ ያሰለፈ የመጀመሪያው ፓርቲ ነው። ወጣት ሴቶች በከተማውና በገጠሩ በርካታ ገድሎችን አስመዝግበዋል። የኢትዮጵያ ሴቶች የትግል ምሰሶ መሆናቸውን ኢሕአፓ አሳይቷል። የጀግና እናት ብቻ ሳይሆን የጀግንነት ቋትና መከሰቻ መሆናቸውን አሳይተዋል። የቤት እመቤት ብቻ ሳይሆን የትግሉም እመቤት መሆናቸውን በኢሕአፓ የተሰለፉ እናቶችና ወጣት ሴቶች አስመስክረዋል።*

*በምርኮኛ መጽሐፍ የቀረቡት እህቶቻችን ታሪክና ተጋድሎ ለዚህ ምስክር ነው። ከእናቶች የበላይሁን እናትና ወ/ሮ ስርጉት ልጆቻቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለሀገራቸውና ለምስኪኑ ሕዝብ መብት መጎናጸፍ የሚያደርጉት ጥረት ተካፋይ በመሆን ድጋፍ ሰጥተዋቸዋል። በወቅቱ በርካታ እናቶች የልጆቻቸውንና የፓርቲውን ዶክመንቶች በጥንቃቄ ከማስቀመጥ አልፈው በዑውታ ኮሚቴ ሙሉ ተሳትፎና ትብብርም አድርገዋል።*


PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በርካታ ወጣት ሴት እህቶቻችን የፍሬሕይወት የትግል ታሪክና የእስር ቤቱን ስቃይ ተጋርተዋል። የሚሚን የአሲምባ ጀግንነት ተጋርተው እዛው ያሸለቡና በሕይወት ተርፈው ለዛሬ ምስክርነት የሚበቁ በርካታ አሉ። የተንደላቀቀ ሕይወታቸውን በወቅቱ አገላለጽ መደባቸውን የሸጡና ለሕዝብ መብት ተሟጋች የነበሩ እንደ ምርኮኛው ሄዊ በርካታ ሄዋኖችን ኢሕአፓ አሰልፏል። የእመቤትን ጠባሳ የተሸከሙ፣ በዓላማ ጽናታቸው የሚስጥረን ጠንካራነት የራሳቸው ትዝታ አርገው የሚወስዱ እህቶቻችን በርካታ ናቸው። በወቅቱ የተጋለጡና መሄጃ ያጡትን መጠለያ በመስጠት ለዛሬ ሕይወታቸው መቀጠል እንደ መልካም ሰውና አመለ ዓይነት ሽፋን ሰጪ የቤት እመቤቶች የትግሉ አካልና የታሪኩ ተቋዳሽ ናቸው። ዛሬ በሕይወት ተርፋችሁ የቆንጂት ብርሃንን ፈለግ ተከትላችሁ የዚያን ትውልድ ታሪክና የራሳችሁን ገጠመኞች የምታስነብቡን በርካት እህቶቻችን ብዕራችሁን እንደምታነሱ ተስፋ አደርጋለሁ።

➢ <u>**የሀሳብ ልዩነት**</u>

በመለስተኛና ጥቃቅን ጉዳዮች ተግባብቶ በአንድነት መጓዝ ሲቻል ልዩነቱን በማክረር እንዴት አለመግባባትና ቡድናዊ ስሜት እንደሚፈጠር ምርኮኛ ገና በጅምሩ በዕድገት በሕብረት ዘመቻ ላይ በመጣው አገልግል አስታካ የምትለውን አገላለጽ ገጽ 44 እንመልከት፤

**ወደ አዲሱ ቤት ለመዘዋወር ዝግጅት ተደረገና ዕቃዎቻቸውን አስረው ማጓጓዝ ጀመሩ። በግልጽና በቃላት አይነገር እንጂ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በአገልግሉ ጉዳይ በተደረገው ስብሰባ ወቅት የተፈጠረውን የሀሳብ መስመር የተከተለ ነው። በአዲሱ ቤት ቦታ ሲያዝ <u>እንደመጀመሪያው ዕለት እንደተገኘ ሳይሆን እየተመራረጡ ሆነ። የቡድን ስሜት ነገሰ፤</u> በጥቃቅኑ ጉዳይ ላይ ሁሉ ግጭቶች ተስተዋሉ። አንዳንድ ጊዜ እንደቀልድ የተጀመሩ ነገሮች ይካረሩና ፈር ይስታሉ። ግጭቶቹ አንዳንዴ መደባዊ ይዘት ያላቸው ይመስላሉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አካባቢያዊ ይሆኑና በአዲስ አበባ ልጆችና በአካባቢው ልጆች መሀል የተከሰቱ ልዩነቶች ይሆናሉ።…**

በ1967 ነሐሴ መጨረሻ እራሱን ኢሕአፓ ብሎ ለሕዝብ ያስተዋወቀው ፓርቲ ብዙም ሳይጓዝ በውስጡ የተፈጠረው የሀሳብ ልዩነትና የቅራኔ አፈታት ደካማነት ችግሩን ወደ መስመር ልዩነት አሻግሮ ፓርቲው ከውጭ ጠላት ባላነሰ የእርስ በርስ ሹኩቻው እንደጎዳው የሚዘነጋ አይደለም።

ምርኮኛ ይህንን አሳዛኝ ልዩነት ስታስታውሰን የአንተነህ በአንጃነት መፈርጅ አብረው ያሉት ጓዶቹ (በላይሁን፣ ፍሬና ሄዋን) ሊቀበሉት ይተናነቃቸዋል። በላይሁን ስለ አንተነህ (የኮድ ስሙ ዓለም) ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሲገልጽ፤ (ገጽ 172)

**"ዓለም የሀሳብ ልዩነት ሊኖረው ቢችል እንኳ በምንም መልኩ በጠላትነት ሊቆም አይችልም"** ነበር ያለው።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ቀስ በቀስ ሁኔታው ያስከተለውን መረበሽ ምርኮኛ በበላይሁን አንደበት እንዲህ ይናገራል (ገጽ 172)፤

*…ጠንካራ የነበረ የመተማመን መንፈስ ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ መጠራጠር በቦታው እየተተካ ሲሄድ አስተውሏል።… በተቻለ መጠን የስብሰባ ቦታዎች መቀያየር እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል። የነበሩት የስብሰባ ቦታዎች ከፓርቲው ጋር የሀሳብ ልዩነት ፈጥረው የተለዩት አባላት በሙሉ ያውቋቸዋል፤…"<u>እርስ በርስ መጠፋፋት ሊመጣ ይሆን እንዴ?</u> እያለ ራሱን የሚጠይቅባቸው ጊዜያት እየበዙ መጥተዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች የታዘባቸው ክርር ያሉ አስተያየቶች ስጋት ላይ ይጥሉታል…*

አንተነህ በበኩሉ ለፍቅረኛው ፍሬሕይወት አንጃ በመባሉ የስሜቱን ያጫውታታል፡

ገጽ 185 …**ድርጅቱን ከራሴም አስበልጬ የምወድ መሆኔን! የማደርገውን ሁሉ የማደርገው ለዓላማና ለድርጅት ስል እንደሆነ እንድትረጂልኝ ብቻ! ሊፈጠር የሚችለው ክፉ ነገር ሲፈጠር ግን እዚህ ሆኜ ማየት አልፈልግም**…"

በዚህም ሊቀበለው ባልቻለው ስያሜና ከአቅሙ በላይ በሆነ ውሳኔ ሀገር ለቆ ሊሰደድ በቅቷል።

በአንጃነት ተሰልፈውም ከመንግሥት የወገኑት የሚያውቁትን የፓርቲውን አሠራርና መረጃ አሳልፈው መስጠታቸውን ቀጥለዋል ምርኮኛ ገጽ 173

…**መረጃዎች በሙሉ ተስፋ የሚያስቆርጡ ከሆኑ ሰንብተዋል፤ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሞቱ፤ ታሰሩ እና ጠፉ የተባሉትን አባላት ቁጥር ሲያስበው ልቡን ከበደው። ከአዲስ አበባ እንዲወጡ ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው የሚቀርቡ አባላት ቁጥር ከአቅም በላይ ሆኗል። በየጊዜው ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገባቸው መሆኑ የሚነገራቸው አባላትም እንዲሁ ተበራክተዋል። እናም ማን ምን ሁኔታ እንደሚያጋጥመው ማወቅ አይቻልም፤ ሁሌም በተጠንቀቅ መንቀሳቀስ ግድ ሆኗል።**

ፍርዬ ተስፋ ቆረጠች

ገጽ 175 "**ከዚህ በኋላ ከማን ጋር ነው የምንሠራው? አብረውኝ ከነበሩ የኮሚቴ አባላት የቀረነው ሁለት ብቻ ነን፤ ከበላይ አካል ጋር የነበረን ግንኙነት መቋረጡ ነው**…"

ገጽ 180 …**እነዛን እንደእግዚአብሔር ታያቸው የነበሩትን ሰዎች ስታስባቸው፡ በእነርሱ መሀል እንዲህ ዓይነት መከፋፈል ይፈጠራል ብላ መቀበል አቃታት። መሠረታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የጠበቀ ትስስር ያላቸው ሰዎች ያን መሠረታዊ ዓላማ ለማስፈጸም መከተል በሚገባቸው ስልት ላይ መግባባት አቅቷቸው ድርጅቱን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ይከፋፈላሉ ብላ ለመገመት ተቸገረች።…ከሁሉም በላይ ሰላሟን ያሳጣት በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል ነው። መተማመን በሌለበት ጥርጣሬ ጉልበት ያበጃል፤ መጠራጠር ደግሞ ኃይልን ይሸረሽራል። እርምጃው ሁሉ ወደሞት የሚጣደፍ ሆኖ ተሰማት።**



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ፍርዬ ከብዙ መከራና ስቃይ በኋላ ከእስር ወጥታም የት ትድረስ ያላወቀቻት እህቷ ሚሚ ድቅን ትልባትና እዚያም ያለውን ሁኔታ በዚህ መልክ ምርኮኛ ታስቀምጠዋለች፤

ገጽ 271…**አሲምባ የኢሕአፓ ሠራዊት አባላት የትጥቅ ትግል ማዕከል መሆኑን ከመስማት ሌላ ስለቦታው የምታውቀው ባይኖርም በሀሳቧ ታየዋለች። በፊልም እንዳየችው የጦር ምሽጎች ሁሉ የአሲምባም ሕይወት ከባድ እንደሚሆን ታስባለች። የተጎሳቆሉ ግን ጠንካሮች ለምንም የማይበገሩ የሠራዊቱ አባላት በአይነ ህሊናዋ ይታዩዋታል፤ ሚሚን ጸጉሯን አሳጥራ፤ ቁምጣ ለብሳ፤ ዝናሯን ታጥቃ፤ በረባሶ ተጫምታ በአሲምባ ተራራ ላይ ላይ ታች ስትል፤ ስትታከስ…ላቧ በግንባሯ ሲንቆረቆር…ሌሎቹ ጓዶች ሲያበረታቷት…ድንገት ደግሞ ሌላው ትዝ ይላታል "<u>እዚያም መከፋፈል ተፈጥሮ ይሆን?</u>" ብላ ራሷን ትጠይቃለች። ልክ እንደዚሁ እንደአዲስ አበባው እነርሱም ዘንድ ክፍፍል ሲፈጠር፤ አንዱ በሌላው ላይ መሳሪያ ሲያዞር…ዐይኖቿን ትጨፍናለች ከዚያ በኋላ ያለውን ላለማሰብ አእምሮዋን ለመግታት ትሞክራለች።**…

በኢሕአፓ የትግል ታሪክ የተፈጠሩ አለመግባባቶችና ልዩነቶች ምንጫቸው ምንድነው? ፓርቲው የሀሳብ ልዩነቶችን እንዴት ነው የሚያስተናግደው? ውስጠ ፓርቲ ነጻነቱስ ምን ያህል ነው? የቅራኔ አያያዝ ብቃቱስ? የከተማው ክፍፍል፡ የሚዳው ልዩነት አልበቃ ብሎ በስደት ያለውስ አካል ከ35 ዓመት በኋላ ተከፋፍሎ አንዱ አንዱን ሲወነጅል ምን ለማለት ይቻላል? ድርጅቱ እንኳን አዳዲስ አባላትን ሊስብ ቀርቶ ያሉትም ሲርቁት መሠረታዊ ችግሩ ምንድነው? ይህም ያለመግባባትና የመከፋፈል አባዜ ዓመታት በተቆጠሩ ቁጥር ከማደግ ይልቅ መጫጫት፡ ከመድመቅ ይልቅ መደብዘዝ፡ ከገናናነቱ ይልቅ አሉ እንዴ የመባሉ ሚስጥሩ ገና ብዙ የሚጻፍበት ሲሆን የቆንጂት ብዕር የዳሰሰው ግን ሊሠመርበትና ሊደምቅ ይገባዋል።

## ➢ <u>የቤተሰብ ስሜት</u>

ሜይ ዴይን አስመልክቶ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. (መጽሐፉ 1968 ይለዋል?) በመላው አዲስ አበባ የተካሄደውን ሰልፍ አስታኮ ስለደረሰው እልቂትና መከራ በዚህ መልክ ቀርቧል፤

የወ/ሮ ስርጉት ሦስቱም ልጆቻቸው ለሰልፉ ከቤት ወጥተው ባለመመለሳቸው

ገጽ 126 "**ምነው ወላዲተ አምላክ የልጅን ነገር ስታውቂው! እባክሽን እናቴ ጭንቁን ተመልከቺ፤ ልፋቴንና ድካሜን አስተውይ**…"

ገጽ 127 "…**በርካታ ሰዎች ወጥተው አካባቢውን ሞልተውታል፤ እዚህም እዚያም ቤት ዋይታ ሆኖአል።…ሁሉ ሰው በድንጋጤ በድን የሆነ፤ እንባውም የደረቀበት ይመስላል። እናቶች መሬቱ ላይ ይንከባለላሉ።**

**የበርካታ ቤቶች ደጃፎች የልጆች አስከሬን ወድቆባቸዋል። በተለይ የአንድ ቤተሰብ ሶስት ልጆች ተገድለው ከቤታቸው አቅራቢያ ተጥለዋል። የልጆቹ ወላጆች ራሳቸውን**



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

***አያውቁም፤ አእምሯቸውን ስተው እብድ ብለዋል። ሰዉ የሚያደርገው ጠፍቶት በማለዳው ብርድ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ይንገዋለላል።***"

*በዚህ ዕለት በከፍተኛ* 15 *ቀበሌ* 23 *ግቢ ገብርኤል አካባቢ ከተኙበት ተወስደው በአንድ ቀን የተገደሉት አራት ወንድማማቾች ደምሴ ብርሃኑ* (18 *ዓመት*)*፤ ተፈሪ ብርሃኑ* (16 *ዓመት*)*፤ ህጻን ግርማ ብርሃኑ* (14 *ዓመት*)*፤ ህጻን ሞገስ ብርሃኑ* (12 *ዓመት*) *እና የ*17 *ዓመት የአባታቸው የእህት ልጅ ተስፋዬ መኮንን የዚህ ታሪክ እውነተኛ አካሎች ሊታወሱ ይገባቸዋል።*

*ገጽ* 128"...***እዚህም እዚያም ቀብር ሆነ። ያውም የወጣት ቀብር***! ***እናቶች ደረታቸው እስኪቆስል ደቁት ልቅሶአቸው እጅግ መረረ። በአንድ አካባቢ ብቻ አስር አዳዲስ የቀብር ቁልሎች ተደረደሩ። ማንም ሳያስተባብረው ሀዘንና ምሬት የፈጠረው የተቃውሞ ሰልፍ ተጀመረ። ወጣቶቹ መፈክሩን ያንበለብሉታል እናቶች እንባቸውን እያዘሩ ይቀበላሉ። እንደናቶች አይብዙ እንጂ አባቶችም ሰልፉ ውስጥ ነበሩ።***"

*ጥር* 1969 *ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የካዛንችሱ መኳንንት አዳሙና የዑራኤል ጓደኞቹ መስፍን ይጥና፡ ሰሎሞን አማኑኤልና አመነው ነገደ ዑራኤል አካባቢ የመኢሶን ታጣቂዎች ሲያሳድዷቸው አመነው ነገደ ሲያመልጥ ሶስቱን ገድለዋቸው ቤተሰብ ከምኒልክ ሆስፒታል የእያንዳንዳቸውን አስከሬን በ*250 *ብር በመግዛት በአንድ ቀን በዑራኤል ቤተ ክርስቲያን እጅግ የተጨናነቀ ቁጥር ያለው ሕዝብ በተገኘበት በደማቅ ሰልፍና መሪር ሀዘን ተቀብረዋል። አመነው ነገደ ከዚያ ተርፎ አሲምባ በውጊያ ላይ እንደተሰዋ ይነገራል። ይህም ታሪክ ከላይ ያነበብነው የምርኮኛ ትረካ እውነተኛ ታሪክ ላይ መመርኮዙ መጽሐፉን ታሪካዊ ልብ ወለድ ያሰኘዋል።*

*ከጊዜ ወደ ኪዜ እየከፋ የመጣው የጅምላ ግድያ ተስፋቸውን ያሚጠጠው ወ/ሮ ስርጉት የመጨረሻ ልመናቸው ይህ ነበር፤*

*ገጽ* 189 " ***ምነው ድሉ ቀርቶ፤ ሁሉም ነግር ውድም ብሎ እነርሱ በደህናቸው ወደቤታቸው በተመለሱ***! ***ኧረ ወላዲተ አምላክ ተለመኝ***!"...***ልጆቻቸው የት ይደርሳሉ ብለው ይጠብቁ እንደነበርና አሁን ደግሞ እየሆነ ያለውን ሲያስቡት ሁሌም ይደንቃቸዋል። ምነው የተመኙት ሁሉ በቀረና ልጆቻቸው በሕይወት በቆዩላቸው፤ ክፉ ነግር ባላጋጠማቸው።***..."***ፈጣሪዬ***! ***እውነት ይህ ነገር ሁሉ አልፎ ልናወራው እንበቃ ይሆን***?" ***አሉ።***

*ገጽ* 207 ...***ቀይ ሽብር አገሩን አናወጠው የወላጅ እጣ ፈንታ በየእለቱ እዚህም እዛም የተጣለ የወጣት ሬሳ ማየት ሆነ። ነፍሰጡር እናቶችም ሳይቀሩ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነው ዋይታ ከተማውን ሞላው።***...

*አዎ አልሞትንም ብለን የምንዋሽ የዚያ ትውልድ ፈርጦች በሕይወት ቆመን ያ ሁሉ ነገር አልፎ እናወራዋለን፡ እንተርከዋለን። ወንድምና እህቶቻችን ከአጠገባችን እየተነጠቅን በሸረሪት ድር የተንጠለጠለች ሕይወታችን ለዛሬ በቅታ ይህን ያሳለፍነውን የጀግንነት ታሪክ ለልጆቻችንና ለትውልድ ተርከነዋል ወይስ ማንነታችንን ደብቀን አፍነን ይዘነዋል*? *ከዚያ መከራና ዕልቂት ተርፈን ዛሬ ባለ ድግሪ የሆንን*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በርካቶች ነን፡ እሰየው ግና እነዚያም የሌሉ ወንድምና እህቶቻችን ቢኖሩ ለዚህ እንደማያንሱ ይገባናል? ዛሬ ትዳር ይዘን ልጆች ወልደን ላደጉት ታዳጊዎቻችን ምንስሳና የምንገበገብ በርካታዎች ነን፡ እሰየው ግና እነዚያም ዛሬ የሌሉቱ ወጣቶች እናትና አባት እንደነበራቸውና ዛሬም ቢኖሩ እናትና አባት ሊሆኑ እንደሚችሉ ትዝ እያሉን እናስባቸዋለን ወይስ…? ዛሬ ገንዘቡ ተትረፍርፎልን የተንደላቀቅን በዚያ መከራ ያለፍን ወገኖች፡ መቃብር ላሉቱ ሰማዕታት ቁራጭ ሻማ እንኳ አብርተን እንዘክራቸዋለን ወይስ…? ቆንጂት ብርሃን 33 ዓመት ቅሪት ሆነሽ ለተገላገልሽው ምርኮኛ ልጅሽ ደስ ይበልሽ። እኔ በበኩሌ አኮራሽን እላለሁ።

የኚያ ለዓላማቸው በጽናት የቆሙ ወንድምና እህቶቻችን ስቃይ እንዴት እንደነበር በዚህ መልክ በምርኮኛ ተቀምጧል፤

ገጽ 227 …**እጆቿን በኤሌክትሪክ ገመድ ግጥም አድርገው አሰሯቸው። …ሁለቱንም እግሮቿን በተመሳሳይ ሁኔታ አሰሩ።…እግሮቿን እንድታጥፋቸውና የታሰሩትን እጆቿን በጉልበቶቿ ላይ እንድታሳልፋቸው ተነገራት። የተባለችውን አደረገች፤ ረጅሙና ወፍራሙ ሽመል በእጆቿና በጉልበቶቿ መሀል እንዲገባ ተደረገ።…ከመቅጽበት ሽመሉን ከግራና ከቀኝ ይዘው ብድግ አድረጉት። ጭንቅላቷ ወደ መሬት ተዘቀዘቀና የሽመሉ ጫፍና ጫፍ ሁለቱ ጠረጴዛዎች ላይ አረፉ።…ያንን አስቀያሚ የካልሲ ኳስ ያለምንም ችግር አፏ ውስጥ ወተፈው። የታነቀች መሰላት። የተሰገሰገው የካልሲ ጥቅል እንዳይወጣ አፏን ግጥም አድርጎ በጨርቅ አሰረው።…ግርፉ ተከታተለ እስከወዲያኛው ድረስ የሚያቋርጥ አይመስልም።…"መናገር ስትፈልጊ ጣትሽን አሳይ" አላት መግረፉን ሳያቋርጥ። <u>"ምንድነው የምናገረው? እከሌ እከሌ እያልኩ የሰው ስም ልዘረዝር በፍጹም አላደርገውም"…"እስከሞት ድረስ እንኳ ቢሆን" ብላ ለራሷ ደመደመች</u>።**

በጠላት እጅ ወድቀው ለድብደባና ለስቃይ ሳይበገሩ ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱ ወገኖቻችን በርካታ ናቸው። በነሱ ስቃይ፡ በነሱ ጠባሳ በነሱ ሕይወት እኛ ኖረናል። ገዳይ መርዝ የዋጡ፡ ከፎቅ የተወረወሩ፡ ሽንት ቤት የገቡ፡ እራሳቸውን ያነቁ፡ ተታኩሰው የሞቱ… ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝብ ነጻነት ለትግል ቤታቸው ኢ.ሕ.አ.ፓ ሲሉ "ቢወቀጥ አጥንቴ" ዘምረው አጥንታቸውን የቀጠቀጡ፡ "ቢንቆረቆር ደሜ" አዚመው ደማቸውን ያንቆረቆሩ ቤቱ ይቁጠራቸው። "ለትግሉ ነው ሕይወቴ" ብለው በፍጹም እምነታቸው ሕይወታቸውን ያስረከቡ የትውልድ ብርቅዬዎች ሁሌም ይታወሱ! ሁሌም ይዘከሩ!

- **<u>ሕይወት እንደገና</u>**

**የከተማው ሕይወት መረጋጋት ይታይበታል፤ እነዚያ በየምሽቱ የሚሰሙ የጥይት ድምጾች የሉም፤ ሳይታሰቡ የሰውን ግቢ በርግደው ቤት የሚያተረማምሱ አሰሳዎች ቀርተዋል። በየመንግዱ ድንገት የሚደረጉት ፍተሻዎች ተቋርጠዋል። ትምህርት ቤቶች ተረጋግተው ትምህርት ቀጥለዋል፡፤ አዲስ አበባ ጸጥ ብላለች።** ገጽ 270

በወጣት ደምና አጥንት ፋሺዝም ለጊዜውም ቢሆን እፎይታ አገኘ። እናቶች ልጆቻቸውን ተነጥቀው ማልቀስ እንኳ ተከለከሉ። ሕጻናት የወንድሞቻቸው ደም ላይ "ድል በድል እየተጎናጸፍን፤ አብዮታችን ግቡን ይመታል! ግቡን ይመታል!"


PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እንዲዘምሩ ተገደዱ። መላ ሕዝብ ሀዘኑን ግራ እጁን ከፍ አርጎ እንዲያደምቅ ተገደደ። አለቀ። ደቀቀ።

በቁጭት የተንገበገቡም ቢኖሩ ትግሉን ለመቀጠል ብዙ ውጣ ውረድ እንድሚገጥም ሳይታለም የተፈታ ነበር። ፈቃደም ከነዚሁ አንዱ ነበር፤

ገጽ 259 "**እና መጨረሻው ምንድነው? ያለቁት አልቀው፤ በአካልና በመንፈስ የተጎዱት ተጎድተው…አጋጣሚ ያተረፋቸው ተርፈው መፈታት? ከዚያስ? በቃ ሕይወት ወደነበረበት መመለስ?..." ለሚደረድራቸው ጥያቄዎች መልስ የለውም። ግራ ይገባዋል፤ የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው እየሆነ በመመልከቱ ይገርመዋል። እርሱ በፍጹም ይህንን አልጠበቀም፤ ትግሉ ቢራዘምም፤ መስዋዕትነቱ ቢበዛም መጨረሻው ድል መሆኑን ተተራጥሮ አያውቅም።…"ይህን ጊዜ እኮ ትግሉ ቀጥሏል። እንደድሮው ጠንካራ ላይሆን ይችላል። ከመታሰር የተረፉት ጥቂቶችም ቢሆኑ፤ ሁኔታው በቀላሉ ባያንቀሳቅስም የበለጥ ሕቡእ መሆን ቢያስፈልግም ትግሉ ግን ይቀጥላል…" ይላል ለራሱ።…የአብዮቱ መክሸፍ ይቆጨዋል "ዓላማችንስ? እንዲቋቋም የምንፈልገው ሕዝባዊ መንግሥትስ? ሕይወታቸውንና አካላቸውን የከፈሉት ጓዶችስ…"እራሱን እስኪያመው ድረስ ያስባል።**

በጅምር መልኩ አይቀጥል እንጂ፡ መሠረታዊ የሀገሪቷና የሕዝቡ ችግሮች እስካልተፈቱ ድረስ የመከራው ገፈት ዋነኛ ቀማሽ መታገሉ አይቀሬ ነበር። ሕዝብ መብቱን እስካላገኘ፡ በሀገሩ ህልውና ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት ካልቻለ፡ ህጻናት ጠግበውና ፈንጥዘው በእንክብካቤ ማደግ ካልቻሉ፡ የትምህርትና የሕክምና መብት እስከተጓደለባቸው ትግል አይቀሬ ነው። ወጣቶች ታፍነው በዓይነ ቁራኛ የሚጠበቁበት አምባገነናዊ ሥርዓት እስካለ ድረስ በበዳይና ተበዳይ መሀል ትግል አይቀሬ ነው። ትግሉም ረዘመም፡ መረረም፡ አስከፊም ሆነ ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ የልጆቿ መሆኗ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

የዚያ ትውልድ ታሪክና ተጋድሎ ለታሪኩ ባለቤቶችና ለደራሲያን እንዲሁም ለተመራማሪዎች የማያቋርጥ፡ የማይነጥፍ መዝገብ ነው። የኢሕአፓን የትግል ታሪክና ተመክሮ ብዙዎች ትምህርት ሊቀስሙበት ይገባል። ምንም ተመክሮ ሳይኖረው ከድክመቱም ከጥንካሬውም የተጋራ ፓርቲ ነውና ይህ ለሀገር አንድነት ለቆሙና ለህዝብ መብት ተሟጋች ለሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች መቃኘት ያለበት ማኅደር ነው። ያለምንም ማጋነን በወታደራዊው አገዛዝና በአጃቢዎቹ አጋፋሪነት በአንድ ትውልድ ላይ የደረሰው ግፍና መከራ ተዝቆ የሚያልቅ አይደለም። "ፍጹም ነው እምነቴ፡ የትግሉ ነው ሕይወቴ" ን ከመዘመር አልፈው የተነሱበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዛሬ የሌሉቱ ገና ብዙ ይጻፍላቸዋል። ቆንጂት ብርሃን ይንን በር ከፍታልናለች። በፍራቻ፡ በቸልተኝነት፡ እገዛ በማጣት፡ በሌላ ሌላም ዝም ያልን ልንቀሰቀስ ይገባናል። የኔን ስሜት ብዙዎች በተለይ በከተማው ተጋድሎ የነበራችሁ ትጋራላችሁ ብዬ አስባለሁ፡ መጽሐፉን ሳነበው እጅግ በርካታ የተፈጸሙ ኩነቶች በዓይነ እሊናዬ መጥቷል። እያንዳንዱ ገጸ ባህሪ ከማውቃቸው ጋር እያያዝኩ ነው የተወጣሁት። የሌሉቱ ፊቴ ድቅን እያሉ ሳላስበው በሚወርድ ዕንባ ንባቤን እያቋረጥሁ ማረፍ ግድ ሆኖብኛል። የራሴን ቁስል ቀስቅሳብኛለችና። ስሜቴ መቃብሩን ፈንቅሎ ነው የወጣው። ብርታትን



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ያገኘሁት በሁለተኛ ዙር ንባቤ ነው። በርካታ ቆንጂቶች እጃቸውን ከብዕር በማገናኘት ብርቅዬ ታሪካችንን ለራሳችንና ለልጆቻቸው እንደሚያስነብቡ ተስፋ አደርጋለሁ።

በመጨረሻም በስፋት ባልገባበትም የመጽሐፉ አንድ ጎኑ አስተማሪነቱ ነው። በተለይ በኤች አይ ቪ ህሙማንን እንክብካቤ አኳያ። ምርኮኛ ይህን የበጎ ፍቃደኞች የቤት ለቤት እንክብካቤ በገጽ 6 እንዲህ ያስቀምጠዋል፤

*…የህሙማን ጉብኝት በማደርግባቸው ቀናት በጎ ፈቃደኞቹ ላስቲካቸውን አሸርጠው፤ ትልቁን ጥቁር ጓንት እጆቻቸው ላይ አጥልቀው የሕሙማኑን ልብስ ሲያጥቡ፤ መጥረጊያቸውን ይዘው አካባቢውን ሲያጸዱ ቆም ብዬ እመለከታቸዋለሁ። አንዳንዶቹ በጎ ፈቃደኞችማ ህሙማኑን አልጋቸው ላይ እንዳሉ የማጽዳት ክህሎታቸው በእነዚህ አጭር ቀናት ተለማምደው የሚሰሩ አያስመስላቸውም፤ የልብ ያደርሳሉ።*

በመንከባከቡ እረገድ በጎ ፍቃደኞች፡ የቤት ለቤት ድጋፍና እንክብካቤ ሰጪ አካላት ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ወጣቶችና ግብረሰናይ ድርጅቶች የሚያደርጉት ጥረት መደነቅ ይገባዋል። የኤች አይ ቪ ህመምተኞች ከኅብረተሰቡ ሳይገለሉ፡ እንደጠያፍ ሳይታዩ እንክብካቤ ይደረግላቸው ዘንድ አርሃያ ለሆናችሁ ወጣቶችና የዚያ ትውልድ ፈርጦች አምሳለ ቆንጂቶች ውለታችሁ አይረሳምና በርቱ።

በጽሁፌ ጅምር ላይ እንደገለጽኩት ይህንን መጽሐፍ የመገምገም ችሎታውም አቅሙም የለኝም። "ያላዋቂ ሳሚ …" እንዳይሆንብኝ ግምገማውን ለባለሙያዎቹ ከስነ ጽሁፍና ቋንቋ አጠቃቀም አንጻር ይገመግሙት ዘንድ እተወዋለሁ። ሆኖም በእኔ ስሜት ቢሆን ጥሩ ነበር የምለውንና መጽሐፉ በልብ ወለድ መልክ ቢቀመጥም እውነተኛን ታሪክ ምርኩዝ በማድረጉ አንዳንድ ሀሳቦችን ማስቀመጡ የመጀመሪያዋ መጽሐፍ ለሆነው ቆንጂት ገንቢ መሆኑን አምንበታለሁ።

## አንዳንድ አስተያየት

### ❖ የሮቤል ድምዳሜ

ሮቤል የቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ ሲሆን ዕድሜውም በስምንት ዓመት እገምተዋለሁ። ፍርዬ የስምንት ዓመት ታናሿ ሲሆን በዘመቻ ወቅት ፍርዬ የ11ኛ ክፍል ተማሪ ከሆነች ቢያንስ 16 ዓመቷ ነው ከሚል ቀላል ስሌት በመነሳት ነው።

ሮቤል ሕይወቱ አስቸጋሪና ምስቅልቅል እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው። በየቀኑ የማይጠፉ እህቶቹና ወንድሙ ከቤት እየራቁ ሲሄዱ፡ ቤቱ ጭር ሲልበት እንደ አዋቂ ባያወራውም ውስጡ እንደሚብሰለሰል መገመት አዳጋች አይደለም። "…እማዬ እራበኝ…ኩርምት ብሎ ተቀምጦ…እማዬ አልቅሰሻል እንዴ…የቤተሰቡን ምስል ሊሥል…ቤቱ ጭር ሲልበት ሬዲዮና ቲቪ በአንድ ላይ ከፍቶ…" ወዘተ የሚሉት አገላለጾች ምንኛ ውስጡ እንደተጎዳና በእድገቱ አሉታዊ ጫና እንደሚኖራቸው መገመት ይቻላል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ስለ ሮቤልና ፍሬ ግንኙነት ምርኮኛ ገጽ 245 እንዲህ ተቀምጧል፤

“ፍሬን የሚመለከታት ልክ እንደናቱ ነው፤ ከልጅነቱ አንስቶ ሁሉን ነገር የምታደርግለት እርሷ ነበረች። ሰውነቱን የምታጥበው፡ ልብሱን የምታለብሰው፡ ከእናቷ ጋር ገበያ በሄደች ቁጥር ካናቴራና ካልሲ የምትገዛለት፤ ብርቱካን፤ ሙዝና ብስኩት የምታመጣለት ፍሬ ነበረች። ከትምህርት ቤት ሲመጣ መክሰሱን የሚጠይቀው እርሷን ነበር። ትምህርት ቤት የምታስመዘግበው ለአንዳንድ ነገሮች የምትሄድለትም እርሷ ነበረች። ዘመቻ የሄደች ጊዜ እንዴት ትናፍቀው እንደነበረ አስታወሰ። አሁንም እንባው በዐይኖቹ ሞላ።”

ይህ ግንኙነታቸው ከእህትነትም አልፎ የእናቱ ያህል ናት ፍሬ ለሱ። በስተመጨረሻም ሚሚ ሄዳ፡ እናታቸውና ቃለአብ አርፈው አጠገቡ ያለችው ፍሬ ብቻ ነበረች። በሀገራችን ባህል ታላቅና ታናሽ ይከባበራል፤ ልጆች እናትና አባታቸውን ያከብራሉ ይወዳሉ። በመካከል የከፋ ቅያሜ ቢኖር እንኳ ያገሬ ሰው “የዘመድ ጥል ...” እንዳለው አይጨካከኑም።

ሮቤል በህጻንነት ዕድሜው ከደረሰበት ስነልቦናዊ ጠባሳ ተጨምሮ በውጭው ዓለም አስተዳደጉ ያሳለፈውን የልጅነት ዘመን እንዳያስብ አድርጎታል ማለት ይቻላል። እህቱን ፍርዬ ታረቀኝን ባለማግባቷ ተቀይሞ ጣምራ እህትና እናት የሆነችው ፍርዬ ላይ እስከመጨረሻው ሊጨክን ያደረገው ጉዳይ ከቶም ቤተሰቡንና ሀገሩን ላለማስታወስ ከሚያደርገው ሙግትም የመነጨ ሊሆን ይችል? ቅያሜም ቢኖረው ያውም የከፋ አይደለምና እንኳን ታማ የአልጋ ቁራኛ ሆና አይደለም ከቤተሰቡ ለሱ ያለችው ሁለመናውን ከሀገር ከወጣበት ጊዜ አንስቶ ለማሰብ አለመፈለጉ ምን ያህል የህፃንነት አስተዳደጉ ሀገሩን እንዳያይ ተጽዕኖ እንዳሳደረበት ጠቋሚ ሊሆን ይችላል።

## ❖ <u>ሜይ ዴይ</u>

በሀገራችን ሜይ ዴይ ብሔራዊ ባህል ሆኖ መከበር የተጀመረው ባልሳሳት በ1968 ዓ.ም. ይመስለኛል። ኢ.ሕአ.ፓ በ1967 ነሐሴ ፕሮግራሙን ለሕዝብ ይፋ ካደረገበት በኋላ የ1968ቱ ሜይ ዴይ በደማቅ ሁኔታ በአብዮት አደባባይ ተከብሯል። በዚሁ ሰልፍ ላይ ኢ.ሕአ.ፓ በየአካባቢው ያሉትን አባልቱን ሲያዘጋጅ ሰንብቶ የሜይ ዴይ ዕለት (ሚያዝያ 23) አብዮት አደባባይ በኢ.ሕአ.ፓ አርማና ወቅታዊ መፈክሮችና በተለያዩ መዝሙሮች ታጅበው ዕለቱን ቀውጢ አድርገውታል። ከተለያየ አካባቢ የመጣውም የኢ.ሕአ.ፓ ሰልፈኛ በወቅቱ በነበሩት የደርግ አመራሮች በነተፈሪ ባንቴ፡ መንግሥቱ ኃ/ማርያምና አጥናፉ አባተ ፊት የኢ.ሕአ.ፓ አርማና ወቅታዊ መፈክር እየተንኾጎደጎደ የታለፈበት ወቅት ነበር። በአጠቃላይ ኢ.ሕአ.ፓ በአጭር ጊዜ ማንነቱንና የፖለቲካ የበላይነቱን ያሳየበት ቀን ነበር። በእርግጥ በወቅቱ በርካታ ወጣቶች ታስረዋል፡ ተደብድበዋል።

ቀጣዩ 1969 ዓ.ም. ትግሉ የተፋፋመበትና ኢ.ሕአ.ፓም በከባድ ፈተና ውስጥ የገባበት ወቅት ነበር። በተለይ ከጥር 24 1969 ዓ.ም. የነተፈሪ ባንቴ ግድያ ወዲህ እየተፋፋመ የመጣው ነጻ እርምጃና አሰሳ፡ ከድርጅቱ ካፈነገጠው አንጃ ጋር ተጣምረው ፓርቲው እጅግ ፈታኝ ሁኔታ መጋፈጥ የተገደደበት ወቅት ነበር። በመሆኑም የሜይ ዴይ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

1969 ዓ.ም. በዓልን ደርግ በተቻለው አቅሙ ያለምንም ተቃውሞ ሙሉ በሙሉ በቁጥሩ ሥር አድርጎ ሊያከብር ተዘጋጅቷል። ይህ የደርግ የኃይል ሚዛን መድፋትና ጭካኔ ምክንያት በማድረግ፡ ፓርቲው ሜይ ዴይ ከሚከበርበት ዋነኛ ቀን ሁለት ቀን ቀደም ብሎ (ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም.) እንዲከበር ወስኖ አከባበሩም በየአካባቢ በሚደረጉ ሰልፎች በአንድ ቀንና ሰዓት በተቀናጀ መልኩ ነበር የታሰበው። ሆኖም ደርግ ሙሉ ቅድመ መረጃ ከአንጃው ክፍል ደርሶት ቀንና ሰዓቱን በየቦታው መጠባበቁ ሳይታወቅ ሰልፉ ተካሄደ፡ እጅግ በአሳዛኝ ሁኔታ በዚያች ቀንና ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ሞቱ። በርካታ አካለስንኩል ሆኑ ለእስር የተዳረጉትም ቀላል አልነበሩም።

የምርኮኛ የአዋሬው የአካባቢ ሰልፍ የገጽ 118 ትረካ በሜይ ዴይ 1968ቱ ሳይሆን በ1969 ዓ.ም. መሆኑን መጠቆም እወዳለሁ።

## ❖ የመጽሐፉ ድምዳሜ

የመጽሐፉ ድምዳሜ ፍሬሕይወት ሲጀመርም መሞቷን ነግሮን ማስነበቡን በመቀጠሉ ሌላ የምንጠብቀው የለም። ባለቤቷም ፈቃደ ሞተ። በላይሁን ሞቷል። አንተነህ እራሱን ስቶ ሆስፒታል ተኛ። ዳኙና ሚስጥረም ኑሮአቸውን ተያይዘዋል። ታረቀኝም እንዲሁ።

በ1966 የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ በወታደራዊው አገዛዝ ከተቀማ ጀምሮ አሁን ባለውም አገዛዝ በትንሹ ለ37 ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን አጥቶ በረሀብ በበሽታና በድንቁርና እየማቀቀ ያለ ነው። ለዚህም መብቱን ለማስከበርና በሀገሩ እንደሁለተኛ ዜጋ እንዳይታይ አንዴ ደመቅ አንዴ ቀዝቀዝ ይበል እንጂ እየታገለ ነው። የ1997 ዓ.ም. የምርጫ ትግል የዚሁ አካል ነው።

ምርኮኛ ያን ትውልድ ታሪክ ስታስነብበን የትግሉ መሪ ድርጅት የነበረው ኢሕአፓ ታሪክ ዋናው ነበር። ነውም። ይህ ፓርቲ በተደጋጋሚ በደረሰበት ጥቃት ብዙ ተጎድቷል። የኢትዮጵያን አንድነት የማይፈልጉ ኃይሎች በአገኙት አጋጣሚ ኢሕአፓ ላይ ይዘምታሉ። የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት እንደልባቸው ሊበዘብዙና ህዝባችንን በባርነት ሊያማቅቁ የሚፈልጉ ባዕዳን ኃይሎች ኢሕአፓ አይመቻቸውም። በ1970 ዎቹ በተደረገው የጅምላ ጭፍጨፋ እጃቸው በደም የተጨማለቀ የቀይ ሽብር ተዋንያንና ገዳዮች ኢሕአፓ ሲባል ዳግም እንዴት እንደሚገድሉት ያስባሉ። ያውጠነጥናሉ። ይህን ሁሉ ችሎ ግን ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ የተዳፈነ እሳት ሆኖ አለ። በደም ውስጥ ያለ ታሪክ ነውና እንሸሸው ብንል አንሸሸውም። የትላንት እናቶች አባቶች የዛሬ አዛውንቶች የራሳቸው ትዝታ አላቸውና። የትላንት በርካታ ሮቤሎች የዛረ ትውልዶች በየቤታቸው ያለቁትን እነፍርዬን፡ ሚሚንና ቃላብን ያስባሉና ታሪኩ ታሪካቸው ነው። የታሪኩ ቀጥተኛ ተሳታፊ ባለቤቶች የዚያ ጊዜ ወጣቶች የዛሬ አባትና እናቶች በተለያየ መስክ ቢጠመዱም ስሙ ሲነሳ ሰውነታቸውን ይነዝረዋል። ይህ በህዝብ ውስጥ የተጠነሰሰ ድርጅት ኮምጠጥ ቢልም አለ። የመጽሐፉን ደራሲ መብት መጋፋት አይሁንብኝና የምርኮኛን ድምዳሜ ታዲያ ስቃኘው ምነው ሚሚን እንኳ ከአሲምባ በሕይወት ተራፊ አድርጋት ወደ ስደቱ ዓለም



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ገብታ ለኢሕአፓ ተሚጋችና የሜዳውን ምርኮኛ ታሪክ ደግም በቀጣይነት ጸሐፊ ባረገቻት ብያለሁ።

**ውድ አንባቢያን፡** በምርኮኛ መጽሐፍ በርካታ ያላነሳዋቸው ጉዳዮች አሉ። የዚያ ትውልድ አካል በመሆኔ ይበልጥ ሚዛኔ እሱ ላይ ደፍቷል። አቀራረቤ ውስጤን ከተሰማኝ እንጂ መጽሐፉን ከመገምገም አኳያ እንዳልሆነ በድጋሚ ልገልጽ እወዳለሁ። የማልችልበትን ገብቼ አላንቦራጭቅምና።

እህታችን ቆንጂት ብርሃን የመጀመሪያ ድርሰትሽ ለእኔ ውብና ማራኪ ነው እላለሁ። ቀለል ባለ አማርኛና አገላለጽ በርካታ ጉዳዮችን አስታውሰሽኛል። በውስጤ የገነባሽው ሞራል አለ። የማውቀውን ጽንሱን የወንድምና እህቶቼን ታሪክ ሕይወት መዝራት እንዳለብን አነቃቅተሽናል። እጅግ ትልቅ ሥራ ሰርተሻል ልትኮሪበት ይገባሻል። ከዚህኛው ጅምር ሥራሽ ትምህርት በመውሰድ፡ ከማንኛውም አቅጣጫ የሚሰጡሽን ትችቶችና አስተያየቶች ግምት በመስጠት ቀጣይ ውጥንሽን እንደምናገኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

**ቸር ይግጠመን**

**ነሲቡ ስብሐት** (alulla2@yahoo.com)

**ቀን፡ ጥቅምት** 19, 2003 (October 29, 2010)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com